**የአቅዋም መመርያ/POLICY JHC—*የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኛነት ማጠቃለያ***

የMontgomery County የትምህርት ቦርድ በJHC *መመርያ—የልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኛነት* ላይ በቀረቡ ለውጦች ህዝባዊ አስተያየት ይፈልጋል። መመርያው Montgomery County Public Schools (MCPS) ለተጠረጠረ የልጅ ማጎሳቆልና የተማሪዎች ቸልታ ማወቅ/መለየት፣ ዘገባ፣ እና መከላከል የሂደት ቅደም ተከተሎችና መመርያዎች አመራር ይሰጣል።

የመመርያውን ክለሳዎች ቦርዱ ሰኞ (ኤፕረል 27፣ 2015) ለጊዜው አፅድቋል የህዝብ አስተያየትም እስከ ጁን 8፣ 2015 በመቀበል ላይ ነው። ቦርዱ የመመርያውን የመጨረሻ ማፅደቂያ በጁን 29፣ 2015 ስብሰባው እንዲሰጥ ይጠበቃል።

የአቅዋም መመርያ/Policy JHC ክለሳ አስፈላጊነት የሚከተሉትን ለማረጋገጥ ነው:-

- ሁሉም ሰራተኞች በባህርያቸው የሚያሳዩትን ከፍተኛ የስነምግባር ደረጃ ማወቅና ተጠያቂ መሆን እንዲሁም የሚያጠራጥር የልጅ መጎሳቆልና ቸልተኝነት የመገንዘብ፣ የማሳወቅና የመከላከል ህጋዊ ግዴታ እና ሞራላዊ ሃላፊነት መከተል ይጠበቅባቸዋል።
- የመጎሳቆል እና/ወይም ቸል የመባል ጥቃት የደረሰባቸው ልጆችና ደካማ አዛውንቶች የሚረዱበት ሁኔታ እንደሚከተለው ነው፤
- አዲስ እና ነባር ሰራተኞችን የሚያጣራ የሰው ሃይል አስተዳደር ስልትና ሂደት ተዘጋጅቷል፤
- ለMCPS ሰራተኞች የባለሙያ ስልጠና ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሁኗል፤ እናም
- የልጆችን እና የደካማ አዛውንቶችን መጎሳቆልና ቸልታ ስለማወቅ፣ ማወቅ እና መከላከል ለወላጆች፣ የውጭ ኮንትራክተሮች፣ ነጻ አገልግሎት ሰጪዎች እና አጠቃላይ ማህበረሰቡ ግንዛቤን የሚያዳብሩ ዕድሎች ተፈጥረዋል።

አስተያየት መስጠት የሚፈልጉ ግለሰቦች ከሁለት ባንዱ መንገድ በፅሁፍ መመለስ ይችላሉ። መልሶች በፖስታ መላክ ያለባቸው በOffice of the Superintendent of Schools, 850 Hungerford Drive, Rockville, Maryland 20850 አድራሻ፣ ወይም በኢሚይል ወደ boe@mcpsmd.org ነው። ሁሉም አስተያየቶች ከትምህርት ቦርድ እና ከትምህርት ቤቶች ተጠባባቂ የበላይ ተቆጣጣሪ ጋር ይጋራሉ። ለተጨማሪ አገባብ፣ MCPS የተከለሰውን የአቅዋም መመርያ መተግበርያ የደንቦች ረቂቅ በይፋ ለጥፏል።

**አጭር መግለጫ**

<u>የተጠረጠረን የልጅ መጎሳቆልና ቸልታ ማሳወቅ እና ምላሽ አሰጣጥ</u>

የተከለሰው የአቅዋም መመርያ ሁሉም የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች የተጠርጠሩ የልጅ መጎሳቆል ወይም ቸልታ ተግባሮችን ለልጅ መከላከል አገልግሎቶች/Child Protective Services (CPS) እንዲያሳውቁ ይፈልግባቸዋል። ዘገባ ከማቅረብ በፊት፣ የተጠጠረ ማጎሳቆልንና ቸልታን ሀቀኛነት ማጣራት ወይም መወሰን የMCPS ሰራተኞች፣ ስራ ተቋራጮች፣ እና በጎ-ፈቃደኞች ሚና አይደለም። ማጎሳቆል ወይም ቸልታ አከናወኑ ግልፅ እንኳን ባይሆንም፣ የሰህተትም ቢሆን ዘገባ ማቅረቡ ይመረጣል። ተከሳሹ ወንጀለኛ የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ እና በጎ-ፈቃደኛ ሆኖ በሚገኝባቸው ሁኔታዎች፣ CPSን፣ የMontgomery County ፖሊስ መምርያ (MCPD)ን እና የMontgomery County ስቴት የአቃቤ ህግ ፅ/ቤትን ከሚያካትት፣ የካውንቲ ተሻራኪ ወኪል ድርጅቶች ጋር በመመካከር ተጠቂ ወይም ተጠቂዎች የተባሉትን እና የሌሎች ልጆችን ደህንነት ለመጠበቅ የስራ አፈፃፀም ፕላን ይፋጠራል። የተጠረጠረውን ማጎሳቆል የማጣራቱን ስራ የካውንቲው ወኪል ድርጅቶች ይመሩታል። በCPS፣ በMCPD ወይም በሌላ የውጭ ወኪል ድርጅት በሚከናወነው ምርመራ ውስጥ ጣልቃ እንዳይገባ ወይም ምርመራውን አደጋ ላይ እንዳይጥል/እንዳያጨናግፍ ምንም የMCPS የውስጥ ምርመራ አይካሄድም።

<u>ምስጢራዊነት፣ ደህንነት፣ እና ከቂም በቀል መከላከል</u>

ማንም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ እና በጎ-ፈቃደኛ ሆነ ብሎ በመጎሳቆል ወይም የቸልታ ክስ ዘገባ ዝግጅትን አያግድም ወይም ጣልቃ አይገባም። ማንኛውም ግለሰብ፣ በበጎ መንፈስ፣ የማጎሳቆል ወይም የቸልታ ክስ የሚያስታውቅ ወይም በዚህ አይነት ክስ ምርመራ የሚሳተፍ በሜሪላንድ ህግ ከመወንጀል ነፃ ነው። MCPS ማንኛውንም የማጎሳቆል ወይም የቸልታ ክስ የሚያመልክተውን ከማስፈራራት፣ ከወከባ ወይም ከቂም በቀል ለመጠበቅ፣ እና፣ በህግ ምንጩን እንዲገለፅ ካልተፈለገ በስተቀር፣ የአመልካቹን ሚስጢራዊነት ለመንከባከብ ይጥራል።

<u>ሆን ብሎ ማጎሳቆልን ወይም ቸልታን ከማመልከት መቆጠብ ወይም በዘገባ ጣልቃ መግባት</u>

አንድ ልጅ ተጎሳቁሏል እና/ወይም ቸል ተብሏል ብሎ የሚጠረጥር እና ዘገባ ያላቀረበ ወይም ሌላን ዘገባ ከማቅረብ የከለከለ ማንኛውም የMCPS ሰራተኛ፣ ስራ ተቋራጭ፣ እና በጎ-ፈቃደኛ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወሰድበታል። ያ ዲሲፕሊን የአንድ ሰራተኛ ከስራ መታገድ

ወይም መሰናበት፣ የተቋራጭ ስራ መቋረጥ፣ እና የበጎ-ፈቃደኛ ልዩ መብቶች ማጣት ሊያካትት ይችላል። በተጨማሪ፣ ማንኛውም የምስክር ወረቀትና ፈቃድ በስቴት ህግ መሰረት ሊነሳ/ሊሰረዝ ይችላል።

<u>ማጎሳቆልና ቸልተኛነት በሚመለከት ጥሰቶች የሚያስከትሉት ውጤቶች</u>

አንድ የዲስትሪክት ሰራተኛ ስራ ተቋራጭ ወይም በጎ-ፈቃደኛ በማጎሳቆልና በቸልተኝነት ተሳታፊ መሆኑን MCPS ከወሰነ፣ ግለሰቡ የሚደርስበት የዲሲፕሊን እርምጃ በስቴት ህግ መሰረት እስከ እና የሰራተኛ መታገድ ወይም መሰናበት፣ የስራ ውል ወይም የበጎ-ፈቃደኛ መብቶች መሰረዝ፣ እና እንደአግባቡ የምስክር ወረቀት ወይም የስራ ፈቃድ ማጣት።

**ትግባሬ**

ይህን መመርያ ተግባራዊ ለማድረግ፣ MCPS የሚፈፅማቸው፡-

- የማጎሳቆል እና/ወይም ቸልተኝነት ክሶችን ዘገባ አቀራረብና ምርመራ ሂደት ቅደም ተከተሎች ለመመስረት ከካውንቲ ተሻራኪ ወኪል ድርጅቶች (CPS፣ MCPD እና የስቴቱ አቃቤ ህግ ፅ/ቤት) ጋር የጋራ ስምምነት መመስረት።
- የMCPS የልጅ መጎሳቆል ተጠሪዎችን መሰየም እና የማጎሳቆል ተጠቂ ለሆኑ ተማሪዎች የድጋፍ አሰጣጥ ሂደት መመስረት።
- የዚህን የአቋም መመርያ ግንዛቤና አተገባበር በሚመለከት ለMCPS ሰራተኞች ሞያዊ ስልጠና መስጠት፣ እናም ለስራ ተቋራጮችና በጎ-ፈቃደኞች፣ እንደአግባቡ፣ ስልጠናና መረጃያዊ እድሎች መስጠት።
- በት/ቤት ንብረት ከሚገኙ ተማሪዎች ጋር ቀጥተኛ_ ቁጥጥር የሌለው ግንኙነት ላላቸው አዲሶችና የቆዩ ሰራተኞችን፣ የውጭ ስራ ተቋራጮችን፣ እና በጎ-ፈቃደኞችን የማጣራት ሂደቶችን ማዳበር፤
- ሃላፊነት የሚሰማው ጠባይ እና በአዋቂዎችና በተማሪዎች መካከል ተገቢ የስነምግባር ኮድ/ደንብና ሌላ አመራር ጥራት ያላቸው መመዘኛዎች ለMCPS ሰራተኞች ማዳበር፤ እና
- በተማሪዎች ትምህርት እንዲሁም በወላጆች/አሳዳጊዎችና በማህበረሰብ አባላት ስለ ልጅ ማጎሳቆልና ቸልተኛነት ግንዛቤ ማሳደግ።

**ግምገማና ዘገባ**

የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ የሚከተሉትን የሚያካትት አመታዊ ሪፖርር—እናም ተጨማሪ ሪፖርሮች እንዳስፈላጊነቱ—ለት/ቤቶች ቦርድ ያቀርባል፦

- በMCPS ለህግ አስከባሪ እና/ወይም የመከላከያ አገልግሎቶች ወኪል ድርጅቶች የተዘገቡ የተጠረጠሩ የማንሳቆል ወይም የቸልተኛነት ጉዳዮች ቁጥር፤
- በአቋም መመርያ/Policy JHC የተደረደሩ ስልቶች አተገባበር፤ እና
- የልጅ ማንሳቆል ወይም ቸልተኛነትን በሚመለከት በMCPS እና በካውንቲው አጋር ወኪል ድርጅቶች መካከል ስለተከናወኑ የትብብሮሽ ጥረቶች መረጃዎች።